


ቀን፡ ነሐሴ 23 2008 ዓ/ም (29/08/2016)
<u>ለንደን</u>

## ከርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የወቅቱን የሃገራችን ኢትዮጵያ ሁኔታ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ።

### በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

### ሕዝቤን ልቀቅ! (ዘጸ. ፰፤፩)

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ አገዛዝ (የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት ሕ.ወ.ሃ.ት.) ከ25 ዓመታት በፊት የመንግሥት በትረ ሥልጣንን እንደ ፈረኦን ከጨበጠ ማግሥት አንስቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ቀዳሚ ዒላማው በማድረግ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ተጥሶ መንበሩ ላይ የተቀመጠ ፓትሪያርክ በህይወት እያለ ያለውን ከመንበሩ በማባረርና በማሳደድ በምትኩ ከራሱ ጎሳ መርጦ ፖትሪያርክ አድርጎ ሾመ።

ይህ የፖትሪያርክ ሹመት ቀኖናን ቤተ ክርስቲያንን ከመጣስ ባለፈ ፖለቲካዊና ከፖለቲካም የከፋው የዘረኝነት ፖለቲካን (ethnocratic politics) የተከተለ ስለነበር በተቀረው የአገዛዙ የዘረኛ መንግሥታዊ መዋቅሮች እንደረደረገው ሁሉ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥም የዘረኝነት መዋቅር እያደገ ሄዶ ለወደፊት ቤተ ክርስቲያኗንም ሆነ አጠቃላይ ሃገሪቱን ለከፋ አደጋ ያጋልጣል በሚል አብያተ ክርስትያናትም ሆኑ በርካታ መንፈሳዊ አባቶችና ምእመናን እርምጃውን በጽኑ ተቃውመውት ነበር።

በወቅቱ ይህንን ድርጊት ከተቃወሙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያናችን አንዷ ነበረች። ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ተቃውሞዋን በይፋ ካሳየችባችው ወቅቶች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1993 ዓ/ም የወቅቱ ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያናን ለመገብኘት በሚል ለንደን በመጡበት ወቅት የቤተ ክርስቲያኗ አባላት የዘርና የፖለቲካ ተሻሚውን ፓትሪያርክ ባለመቀበል ተቃውመው ከቤተ ክርስቲያኗ እንዲባረሩ ያደርጉበት እርምጃቸው ነበር።

ከዛም በመቀጠል ለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ተራዳኢነትና በአባላቷ ጥንካሬ የኢትዮጵያው ዘረኛ አገዛዝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሊያሳድር ከሚችለው ተጽዕኖ ሁሉ ራሷን ነጻ በማድረግ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃይማኖታዊና ቀኖናዊ ሕግጋትን ጠብቃ ራሷን ስታስተዳድር ኖራለች። ቤተ ክርስቲያኗ በአቋሟ ጸንታ በመቆየትም በአገዛዙም ሆነ በሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖቶ ጠላቶች አማካኝነት በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ገዳማት፤ አብያተ ክርስቲያናትና ተከታዮቿ ላይ በየጊዜው የሚደርሱ በደልና ጥቃቶችን በመቃወምና በማውገዝ ለዓለም ሁሉ አቤት ስትል ቆይታለች።

ይህም ብቻ አይደለም በተለይ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2005 ዓ/ም የሃገራዊ ምርጫን ተከትሎ አያሌ ንጹሐን ዜጎች በዘረኛው አገዛዝ የጸጥታ ኃይሎች ሲገደሉ ከክርስትና እምነት ውጪ በሆነ መንገድ የአገዛዙን ፖለቲካዊ መመሪያ ወደ ቤተ ክርስቲያን በማምጣት አብያተ ክርስቲያናት ለተገደሉት ዜጎች ጸሎት እንዳያካሂዱ የወቅቱ ፓትሪያርክ (ኢትዮጵያ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ) መመሪያ ሲያወጡ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ግን ከዘረኛው አገዛዝ ቀጥተኛም ሆነ የተዘዋዋሪ ተጽኖ ራሷን ነጻ ያደረገች በመሆኑ ለተገደሉት ንጹሃን ኢትዮጵያዊ ዜጎች የተሟሏ የፀሎት መርሃ ግብር አካሂዳለች።

ከዚህ ጋር በማያያዝም ከክርስትና እምነት ውጪ በመሆን ቤተ ክርስቲያን ለሞተ ሰው ፀሎት አታካሂድ የሚል የዘረኛ አገዛዝ ፖለቲካዊ መመሪያ ያወጡትን የወቅቱን ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስን በማውገዝ የአቋም መግለጫ አዘጋጅታ ለዓም ሁሉ እንዲሰራጭ አድርጋለች።

ከዚህ ቀጥሎ የነበረው ክስተት ከአቡነ ጳውሎስ እልፈት በኋላ ለሁለት የተከፈለው ሲኖዶስም ሆነ በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኗ ተመልሳ አንድ የምትሆንበትን አጋጣሚ መፈጠር ነበር። በዚህ ወቅት አያሌ የቤተ ክርስቲያኗ እውነተኛ ልጆች ሂደቱን በታላቅ ተስፋ ሲጠባበቁ የኢትዮጵያው አገዛዝ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያደርገውን ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት በመቀጠል አሁንም በድጋሚ የዘር ፖለቲካን (ethnocratic politics) ተከትሎ ከራሱ ጎሳ መርጦ ሌላ ፓትሪያርክ በመሾሙ ተስፋው

እንዲጨልም ሲያደርግ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ድርጊቱን በመቃወም ከቀድሞ አቋሟ ሳትለወጥ ቀጥላበት ትገኛለች።

ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሃገራችን ዘርን መሠረት አድርጎ የተደራጀው የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት (ሕወሃት) አንባ ገነናዊ አገዛዝ ያንገሸገሻቸውም ሆኑ የሚደርስባቸው የሰብዓዊ መብት መደፈርና የነጻነታቸው መገፈፍ ያስቆጣቸው ኢትዮጵያውያን ተቃውሞአቸውን በሰላማዊ ሰልፍ በሚገልጹበት ወቅት አገዛዙ በአለሞ ተኳሽ የተጠናከረ ወታደራዊ ኃይልና ለሰው ልጆች ህይወት መቅሰፍት የሆኑ የጦር መሣሪያዎችን አስታጥቆ በማሰለፍ እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረውን ክቡሩን የሰው ልጅ ህይወት እየቀጠፉ የሚያደርሱትን ግድያና ጭፍጨፋ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጽኑ ታወግዛለች!!

በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ካለፉት ወራቶች ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በጎንደርና በጎጃም፣ እንዲሁም በሌላ የሃገሪቱ ክልሎች አገዛዙ እስከ አፍንጫው የታጠቀ ወታደራዊ ኃይልን ባልታጠቀ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ በማዝመት በንጹሐን ዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ግድያ ከማውገዝ በተጓዳኝ ለእነዚሁ ህይወታቸውን በግፍ ለተነጠቁ ኢትዮጵያውያን በየጊዜው የጸሎት መርሃ ግብር በማካሄድ ላይ የምትገኝ ሲሆን ይህን በኢትዮጵያ ሃገራችን ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ አረመኔያዊ ግድያና ጭፍጨፋ በመላው ዓለም የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በአንድነት ያወግዙትና ይኮንኑት ዘንድ ጥሪዋን ታስተላልፋለች።

**ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች። መዝ ፷፰፣፴፩**